አላህ ሆይ! ከመጪው አለም ኑሮ ውጪ ኑሮ የለም። ለአንሷሮችና ሙሃጂሮች ማራቸው።

ከአነስ ቢን ማሊክ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈንና- እንዲህ ብለዋል፦ "አላህ ሆይ! ከመጪው አለም ኑሮ ውጪ ኑሮ የለም። ለአንሷሮችና ሙሃጂሮች ማራቸው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ - የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና - እውነተኛ ኑሮ በመጪው አለም በአላህ ውዴታ፣ እዝነትና ጀነት ውስጥ ያለው ነው እንጂ ሌላ ትክክለኛ ኑሮ እንደሌለ ተናገሩ። የዱንያ ኑሮ ተወጋጅ ነው። የመጪው አለም ኑሮ ዘውታሪና ቀሪ ነው። ቀጥለውም ነቢዩ - የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና - ምህረትን፣ መከበርንና መልካምነትን ለእነዚያ ነቢዩን - የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና - እና ሙሃጂሮችን ላስጠጉትና ገንዘባቸውን ላካፈሉት አንሷሮች በተጨማሪ የአላህን ውዴታና ችሮታ ፈልገው ሃገራቸውንና ገንዘባቸውን ትተው ለተሰደዱት ዱዓ አደረጉላቸው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3773